የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ሃ64-02/መ28/82/4

13 ህዳር 2014

**ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**በፍትህ ሚኒስቴር**
**ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር መጠየቅን ይመለከታል፡፡</u>**

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በቦርዱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 መሰረት የተቋቋመ ህዝቦች በየደረጃው በሚካሄድ ነጻ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር እንዲያውሉ ለማድረግ እንዲቻል በአዲስ መልክ የተቋቋመ የዴሞክራሲ ተቋም ነው፡፡ በዚህ መነሻነትም ቦርዱ 6ተኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም እና መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በስኬት ማስፈጸሙ ይታወቃል፡፡ ምርጫው ከተከናወነ በኃላም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ዕጩዎች ከድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ውጤት ጋር በተያያዘ ያላቸውን ቅሬታ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ለቦርዱ በማቅረብ ተገቢውን ሂደት ተከትሎ የምርጫው ውጤት ይፋ አድርጓል፡፡

ከቁጫ ምርጫ ክልል ጋር ተያይዞ በነበረው ምርጫ የቁጫ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ አሸንፎ የነበረ ሲሆን ነገር ግን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ /ኢዜማ/ በምርጫ ወረቀቱ ላይ የፓርቲው የክልል ምክር ቤት ዕጩ አለመካተትን መነሻ አድርጎ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ መነሻነት ምርጫው



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

እንዲደገም ተወሰነ፡፡ ከዚህ ውሳኔ በሃላ ቦርዱ እንደውሣኔው ለመፈፀም በእንቅስቃሴ ላይ እያለ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ /ኢዜማ/ ለክልል ምክር ቤት እንዲወዳደሩ ያቀረባቸው ሁለት ዕጩዎች ከዕጩነት ራሳቸውን ስላገለሉ እና ቀሪ አንድ ዕጩ ደግሞ በፓርቲው ከዕጩነት ስለተነሱ ቦርዱም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሰጠው ውሳኔ አፈጻጸም መመሪያ እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተፈጠረው አዲስ ክስተት ምክንያት ውሳኔውን የማያሻሽል መሆኑን በመግለፅ ቦርዱ እንደፍርዱ ለመፈፀም የማያስችለው አዲስ ሁኔታ አለ የሚል ከሆነ ይህንኑ ጠቅሶ የመሰለውን መወሰን የሚችል መሆኑን ገልፆ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ለዳግም ምርጫ ውሳኔ ምክኒያት የሆኑት የኢዜማ ዕጩዎች በፓርቲውና በገዛ ፈቃዳቸው ከዕጩነት ስለተነሱ ለዳግም ምርጫ ውሳኔ ምክኒያት የሆነው ሁኔታ ቀሪ በመሆኑ ቦርዱ ዳግም ምርጫ ለማድረግ እንደማያስችለው በማመን ይህንኑ ውሳኔ በማስተላለፍ በመጀመሪያው ምርጫ አሸናፊ የሆኑትን የቁጫ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ዕጩዎችን አሸናፊነት አረጋግጧል፡፡

ይህንኑ ውሳኔውን ቦርዱ ይፋ በማድረጉ የጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት የቁጫ ምርጫ ክልልን በሚመለከት ህዳር 8 ቀን 2014 ዓ.ም "ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የቁጫ ምርጫ ክልልን አስመልክቶ ባስተላለፈው የተዛባ ውሳኔን በሚመለከት የተሰጠ መግለጫ" በሚል ርዕስ እና የጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ በተመሳሳይ በህዳር 8 ቀን 2014 ዓ.ም "ጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ከመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ዛሬ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ባስተላለፈው ውጤት ላይ የተሰጠ መግለጫ" በሚል የፌስቡክ ገጾቻቸው ላይ ባወጧቸው መግለጫዎች በ1997ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ወንጀል ህግ እንዲሁም የጥላቻ ንግግርን እና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር

1185/2012 የተላለፈ የወንጀል ተግባር በቦርዱ ላይ ተፈጽሟል፡፡ ለዚህም ማሳያዎቹ፡-

የጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ከላይ በተጠቀሰው መግለጫው፤

1. "የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የህዝቦችን ውሳኔ ለማክበር የተቋቋመ ተቋም ሳይሆን የህዝቦችን ውሳኔ በመጻረር ህዝብ በመንግስት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርግ እንዲሁም በዚህ ፈታኝ ወቅት ህዝብ መንግስት ላይ እንዲያምጽ የተለያየ ስልቶችን እየተጠቀመ የጁንታውን ተልዕኮ ለማስፈጸም የሚኳትኑ ግለሰቦችን የያዘ ተቋም መሆኑ ለማንም የተደበቀ አይሆንም፡፡"
2. "ምርጫ ቦርዱ በቁጫ ምርጫ ክልል ገለልተኛ ያልሆኑ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ከማደራጀት አንስቶ እስከ ድምጽ መሰረዝ አልፎም አሰራርን ያልተከተለ ውሳኔን በመስጠት ህዝብን ክፉኛ እያስቆጣ ይገኛል፡፡"
3. "በሸፍጥ የተካነው ቦርዱ ዳግም ምርጫ ቢካሄድ እንኳን ህዝቡ የሚመርጠው ብልጽግናን መሆኑን በመረዳት ምርጫውን ለማቆየት ሲባል የአካባቢውን ገጽታ በማይገልጽ ሁኔታ የጸጥታ ችግር በመኖሩ ምርጫውን ማስኬድ አልቻልኩም ሲል የተለያዩ የሚዲያ አውታሮችን በመጠቀም የሀሰት ፕሮፓጋንዳን በመንዛት ምርጫውን አቆይቶ ነበር፡፡"
4. "ህዝባችንን ሊወክሉ የሚችሉት በህዝባችን የተመረጡ እንጂ በቦርዱ የተመረጡ ባለመሆኑ ሚዛናዊነት የጎደለውን የቦርዱንና ውሳኔንና ማጭበርበር እንዲሁም ቦርዱ በምርጫ ክልሉ የሚገኘው ህዝብም ያለ ተወካይ እንዳይቀር ብዬ ነው ብሎ ለህዝብ ውግንና ያለው በማስመሰል ያስተላለፈው የሸፍጥ

<u>**ውሳኔ**</u> ህዝባችንን የማይወክል መሆኑን በድጋሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡" የሚሉ ሃሳቦችን በዋናነት ይዟል፡፡

በ1997 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀጽ 613/2 እና 3/ እና 618/መ/ እንዲሁም የጥላቻ ንግግርን እና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1185/2012 አንቀጽ 5 ድንጋጌዎችን በሚተላለፍ መልኩ የፓርቲው ጽ/ቤት ቦርዱ ህጋዊ መሰረት ያለው ምርጫን ለማስፈጸም በህግ የተቋቋመ፤ ስራውንም በገለልተኝነት እያከናወነ ያለ፤ በህዝብ እና በፓርቲዎች እምነት የሚጣልበት ስራ እየሰራ የሚገኝ ተቋም መሆኑን እያወቀ ቦርዱ የህዝብን ውሳኔ ለማክበር የተቋቋመ ተቋም አይደለም፤ የህዝብን ውሳኔ የመጻረር አላማ ያለው በማለት ገልጾታል፡፡ ጽ/ቤቱ በተጨማሪ ቦርዱ አመጽ በህዝብ እንዲነሳ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን እና የፓርቲው መግለጫ ጁንታ ብሎ የሚጠራውን አካል ተልዕኮ የሚያስፈጽሙ ግለሰቦችን ይዟል፤ ቦርዱ በሸፍጥ የተካነ ነው፤ ቦርዱ ለህዝብ ወኪሎቹን የሚመርጥ እንደሆነ አድርጎ ማቅረቡ፤ ግልጽ በሆነ እና ፓርቲዎች ጭምር የተሳተፉበትን የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ ሂደት ያልተከናወነ በማስመሰል ቦርዱ ገለልተኛ ያልሆኑ ምርጫ አስፈጻሚዎችን በምርጫ ክልሉ በሃሰት መድቧል እና በስተመጨረሻም ቦርዱ በቁጫ ምርጫ ክልል በነበረው ምርጫ የሸፍጥ ውሳኔ ሰጥቷል ማለቱ ቦርዱ ከቁጫ ምርጫ ክልል ጋር ተያይዞ የሚሰጣቸውን ማንኛውም ውሳኔዎች እና የሚከተላቸውን ህጋዊ አሰራሮች ዋጋ አልባ ለማድረግ፤ ተቋሙ በከፍተኛ ወጪና ድካም የገነባውን መልካም ስም ላይ ከባድ ጉዳት ለማድረስ በማቀድ፤ ህዝብ ተቋሙና ሰራተኞቹ ላይ ያለውን አመኔታ ለማሳጣት እንዲሁም በተቋሙ የስራ ግዴታቸውን የተወጡ የመንግስት ሰራተኞችን ለማዋረድ ሆን ተብሎ የሃሰት መረጃን

የማሰራጨት፤ ስም የማጥፋት እና የማዋረድ ወንጀል ተግባሮችን የፓርቲ ጽ/ቤት መፈጸሙን መረዳት ይቻላል፡፡ መግለጫው በዚህ መጠን የተሰጠው በተለይም ከምርጫው በፊት የምርጫ ክልሉን ያስተዳድር ከነበረ ከፍተኛ ሃላፊነት ይሰማዋል ተብሎ ከሚጠበቅ ተቋም መሆኑ ህዝብን ለአላስፈላጊ ግጭት እና አመጽ አያነሳሳም/አይዳርግም ለማለት አይቻልም፡፡

በተመሳሳይ የጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ በመግለጫው "በምርጫ ክልሉ ምንም አይት ችግር ሳይፈጠር ችግር አለ በማለት በሰላም የምርጫው ሂደት ተጠናቆ የማዳመር ስራው ቆሞ ወደ ፌዴራል ተጭኖ **<u>የተሸጠውን የህዝብ ድምጽ</u>** እንዲመለስ በሰላም የሰላም አምባሳደር ሰላም ወዳድ በሆነው ጋሞ ዞን በቁጫ ህዝብ ስም እንጠይቃለን፡፡" በማለት ባወጣው መግለጫ መራጩ ድምጹ እንደተሰረቀ እና የድርጊቱ ፈጻሚም ምርጫ ቦርድ እንደሆነ ተደርጎ መቅረቡ ፍጹም ሀሰተኛ የሆነን መረጃ የማሰራጨት ተግባር ነው፡፡

በመሆኑም ቦርዱ ከላይ የተገለጹት ሁለት ተቋማት በመግለጫዎቻቸው አማካኝነት በወንጀል ህጉ እና የጥላቻ ንግግርን እና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ድንጋጌዎች በመተላለፍ የምርጫ ቦርድን እንዲሁም የተቋሙን ሰራተኞች መልካም ስም የማጥፋት፤ ሀሰተኛ መረጃን የማሰራጨት እና የማዋረድ ወንጀሎች መፈጸማቸው ካቀረብነው የጽሁፍ ማስረጃ በማረጋገጥ በፍርድ ቤት ተጠያቂ እንዲደረጉ እና አስተማሪ እርምጃ እንዲወሰድባቸው በማክበር ያመለክታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA



ከሠላምታ ጋር

Woubshet Ay

Deputy Chairperson National Electoral Bo

ጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት

Yesterday at 1:52 AM ·

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቁጫ ምርጫ ክልልን አስመለክቶ ባስተላለፈው የተዛባ ውሳኔን በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

ምርጫ የህዝቦች ሉአላዊ የሥልጣን ምንጭና ህገ መንግስታዊ መብታቸው የሚረጋገጥበት እንጂ የተወሰኑ ግለሰቦችን ለማደላደል የሚሰጥ ስጦታ አይደለም

ምርጫ ቦርድ ትልቅ ኃላፊነት የተጣለው የህዝብ ድምፅ ይከበር መርህ አድርገው የሚንቀሳቀስ ተቋም ስሆን ግን የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በተቃርኖ የቆመ ተቋም መሆኑን በድጋሚ አሳይቶናል። የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የህዝቦችን ውሳኔ ለማክበር የተቋቋመ ተቋም ሳይሆን የህዝቦችን ውሳኔ በመፃረር ህዝብ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርግ እንዲሁም በዚህ ፈታኝ ወቅት ህዝብ መንግስት ላይ እንዲያምፅ የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀመ የጁንታውን ተልዕኮ ለማስፈፀም የሚኳተኑ ግለሰቦችን የያዜ ተቋም መሆኑ ለማንም የተደበቀ አይሆንም ።

ምርጫ ቦርዱ በቁጫ ምርጫ ከልል ገለልተኛ ያልሆኑ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ከማደራጀት አንስቶ እስከ ድምፅ መሰረዝ አልፎም አሰራርን ያልተከተለ ውሳኔን በመስጠት ህዝብን ከፉኛ እያስቆጣ ይገኛል ።

በኢትዮጵያ ህገ መንግስት ከስ ማሻሻል ፤ከስ ማንሳት በህግ የተቀመጠ ብሆንም ይህን ቅድመ ሁኔታ ባልተጠቀመበት በኢትዮጵያ ዜጎች ማህበር /ኢዜማ/ እና በምርጫ ቦርድ መካከል ባለው ከስ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቁጫ ምርጫ ከልል የክልል ምክር ቤት ምርጫ ውድቅ ተደርጎ እንደገና ምርጫ እንዲካሄድ ውሳኔ ማሳለፉ አይዘነጋም ።

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድም የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተቀብሎ ዳግም ምርጫ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ጨርሰው የተፎካካሪ ፓርቲዎች ለዳግም ምርጫ እንዲዘጋጁ ጥሪ በማቅረብ የምርጫ ቁሳቁሶቹን ወደ ምርጫ ክልሉ ማስጫን መጀመሩም አይዘነጋም ። ነገር ግን በሸፍጥ የተካነው ቦርዱ ዳግም ምርጫ ብካሄድ እንኳ ህዝቡ የሚመርጠው ብልጽግና መሆኑን በመረዳት ምርጫውን ለማቆየት ሲባል የአከባቢውን ገጽታ በማይገልጽ ሁኔታ የፀጥታ ችግር በመኖሩ ምርጫውን ማስኬድ አልቻልኩም ሲል የተለያዩ የሚዲያ አውታሮችን በመጠቀም የሀሰት ፕሮፖጋንዳን በመንዛት ምርጫውን አቆይቶ ነበር።

ሆኖም ቦርዱ ህዳር 7ቀን 2014 ዓ/ም ባወጣው መግለጫ በኢዜማ ፓርቲ በኩል በተደረጉ ለውጦች መነሻ ፍርድ ቤቱን ስለተደረገው ለውጥ ማብራሪያ ጠይቀ ከውሳኔው በኃላ የተደረገ ለውጥ ካለ ቦርዱ እንደሁኔታው መወሰን ይችላል ብሎኛል በማለት በህዝብ ያልተመረጡ ግለሰቦች ህዝብን ይወከሉ የሚል ግልጽነት የጎደለ ውሳኔ ሰጥተዋል ።በመሆኑም ቦርዱ ያስተላለፈው ውሳኔ መሠረታዊ የህግና አሰራር ጥሰት ያለው በመሆኑ የቦርዱን ውሳኔ አጥብቀን እናወግዛለን ።

ህዝባችንን ልወከሉ የሚችሉት በህዝባችን የተመረጡ እንጂ በቦርዱ የተመረጡ ባለመሆኑ ሚዛናዊነት የጎደለውን የቦርዱን ውሳኔንና ማጭበርበር እንዲሁም ቦርዱ በምርጫ ክልሉ የምገኘው ህዝብም ያለ ተወካይ እንዳይቀር ብዬ ነው ብሎ ለህዝብ ውግንና ያለ በማስመሰል ያስተላለፈው የሸፍጥ ውሳኔ ህዝባችንን የማይወከል መሆኑን በድጋሚ
ለመግለጽ እንወዳለን ።

👉 አከባቢዎን ይጠብቁ !!
👉 ወደ ግንባር ይዝመቱ!!
👉 መከላከያን ይደግፉ !!

**Gamo Zone Kucha Woreda Government Communication Affairs Department**

16 November at 23:58 ·

ጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ከመንግስት ኮሚኒኬሽን ዛሬ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባስተላለፈው የምርጫው ውጤት ላይ የተሰጠ መግለጫ።
========================================

በመጀመሪያ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም ተደራጅተው የሀገራችንን ሰላም ለማደፍረስ የህዝብ ለህዝብ አብሮነትን ለመበጣጠስ አንድ እናት ሀገራችንን ለማፍረስ እየተንቀሳቀሱ ያሉ እኩይ ስራቸውን በማጋለጥ ብልጽግናችንን እውን እናደርጋለን ኢትዮጵያን ለመታደግ መከላከያ እንደግፋለን:እንዘምታለን:አካባቢያችንን ተደራጅተን እንጠብቃለን!!

ቀን 09/03/2014 ዓ:ም (የቁጫ ወረዳ መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት) እንደምታውቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ 6ኛ ዙር ሀገራዊ ምርጫ አንዳንድ የፀጥታ ችግር ያሉባቸው ከሀገራችን ክፍሎች ውጪ በመላ ሀገሪቱ የምርጫው ሂደት ሰላማዊ: ፍትሀዊና ተአማኒ ምርጫ በተሳካ ሁኔታ ማካሄዷ ይታወሳል።

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ እንደማንኛውም የሀገራችን ክፍሎች 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ 7 (ሰባት ) ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተወዳድረው የምርጫው ሂደት በተከፈቱት 86 የምርጫ ጣቢያዎች የፀጥታው አካል የምርጫ አስፈፃሚዎች እና የየፓርቲዎቹ ታዛቢዎች ህብረተሰቡ በሰላም ድምጹን ሰጥቶ ከጨረሱ በኋላ ተፈራርመው ወደ ማዕከል ምርጫ ቦርድ የምርጫ ኮሮጆዎች ተሰብስቧል።

ይሁን እንጂ የምርጫው ዕለት ሰኞ ማታ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ሂደቱ እስከ ምሽቱ 3:00 ሰዓት ድረስ እንዲካሄድ ትዕዛዝ ተላልፎ በየምርጫ ጣቢያዎች ህዝቡ በሰላም ሰልፍ ላይ ሆኖ ተራውን ስጠባበቅ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች አንዱ የቁሕዴፓ አባላትና ደጋፊዎቹ ምሽቱን ሙሉ ምርጫውን አሸንፈናል በማለት በተዘጋጀላቸው ሆቴል ስጨፍሩ አድረዋል።

በንጋታው ማቅሰኞ ጠዋት ወደ 4:00 ሰዓት ገደማ የምርጫው ውጤት እንዳሰቡት ሳይሆን ከየምርጫ ጣቢያዎች የመጣውን ውጤት ሲዳመር ብልጽግና በአብላጫ ድምጽ እየመራ መሆኑን ወሬዎች መውጣት ስትጀምሩ ጭፈራቸውን ትተውት እንደት ብልጽግና ይመራል በማለት ከስ ወረቀት ይዘው ወደ ምርጫ ቦርድ እና ወደ ተፎካካሪ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጽ/ቤት ይገባሉ።

የምርጫ ቦርዱ ሰብሳቢ ከየጣቢያዎቹ በሰላም ተሰብስበው የመጡትን ውጤቶች በአስፈፃሚዎች, በታዛቢዎች እና በፀጥታ አካላት ፊት የማዳመር ስራ ሰርቶ ለህዝብ ውጤቱን ይፋ ማድረግ ስገባው ሀላፊነቱን ትቶት ሰበብ አስባብ መፍጠርና እንደገና ኮሮጆ ተፈቶ እንዲቆጠር ይደረገና የምርጫ ቦርዱ ሰብሳቢ የቆጠራውን ሂደት ማጓተት ይጀምራል።

በዚህ ሂደትም የምርጫ ቦርዱ ሰብሳቢ የፀጥታ ሀይል ሳይዝ ወደ ኮሮጆው በተቀመጠበት አዳራሽ መግባት እንዲሁም የድምጽ አቆጣጠር ሂደቱን ቁጥር ማሳሳት ጀመረ የተሰጠውን በገለልተኝነት እንዲያገለግል የማለበትን ስልጣን አላግባብ በመጠቀም።

ቆጠራው ሂደት የወረዳው የተፎካካሪ ፓርቲዎች ባሳዩት ትህትናና በፀጥታው አካል ትዕግስት ወደ ማለቁ እየተቃረበ ስሄድ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተደውሏል በአካባቢው የፀጥታ ችግር ስላለ የቆጠራው ሂደት ይቁም የህዝብ ድምጽ ወደ አድስ አበባ ይጫናል ተባለ የምርጫ ቦርዱ ሰብሳቢ ለምን ይሄዳል ያለቀው ይለቅና የህዝብ ድምጽ ይፋ ይሁን ይለጠፍ ተብሎ ስጠየቅ አሻፈረኝ መጫን አለበት ብሎ ወደ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የጋሞ ደሬ ቁጫ ህዝብ ድምጽ ካለ ምንም ችግር ያለቀው ባልታወቀ ምክኒያት ወደ ማዕከል ይወሰዳል ።

አድስ አበባ ሄዶም በገለልተኛ አካላት እና በተፎካካሪ ፓርቲ ተወካዮች ፊት ቆጠራው ተጀምሮ እያንዳንዱን የድምፅ ጣቢያ ኮሮጆ ተከፍቶ ተቆጥሮ ሁሉም ተፈራርመው የቆጠራውን ሂደት ጨርሰው ብልጽግና ፓርቲ በከፍተኛ ድምጽ ማለፉን አረጋግጠው በጊዜው የምርጫ ቦርዱ ኋላፊ(ሰብሳቢ) ወ/ሮ ብርቱካን ሚደቅሳ የለችም እስከምትመጣ ታሽጎ ይቀመጣል ፊርማ ትሰጣቹዋለች ተብለው ተፈራርመው አስቀምጠው ይመለሳሉ።

ከሳምንት በኋላ ድምጹ የኦዲት ችግር አለበት ተብሎ ማንም በለለበት የፌደራል-24 እና የክልል-28 ባጠቃላይ 52 የምርጫ ጣቢያ ተሰርዞ ቁሕዴፓ አለፈ ተብሎ በሚዲያ ተለቀቀ።ጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ክስ ይጀምርና በሂደት ላይ እያለ የኢዜማ በአንድ የምርጫ ጣቢያ የተወዳዳሪ ፎቶ ስላልመጣላት የቁጫ ምርጫ ክልል የክልል ምርጫ ውጤት ላይ ባቀረበው ቅረታ መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምርጫው እንዲሰረዝ ለምርጫ ቦርድ ትዕዛዝ ስተላልፏል።

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተከትሎ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም የቁጫ ምርጫ ክልል የክልል ምርጫ እንደገና እንደሚደረግ ማስተላለፉ ይታወሳል።ሆናም ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ምርጫው መቼ እንደሚደረግ አልተወሰነም በመስከረም 21/2014 ዓ:ም በድጋሚ በሚከናወነው ድጋሚ ምርጫ ጋር የቁጫ ምርጫ ክልል እንደማይደረግ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኩል ይተላለፋል ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስተላለፈውን ውሳኔ ሽሮ የምርጫ ክልሉ ጋሞ ዞን የቁጫ ወረዳ ህዝብ ያለ ተወካይ እንዳይቀር በማለት 52 የምርጫ ጣቢያ የህዝብ ድምጽ በመሰረዝ የቁሕዴፓ የክልል ምክር ቤት ተውካዮች ወደ ምክር ቤቱ ይግቡ በማለት ያስተላለፈው ውሳኔ ትክክለኛ እንዳልሆነ እና የወረዳው ህዝብም ትክክለኛውን የመረጠውን አምኖ የሰጠውን ድምፅ ይጠብቃልና ባልመረጠው አካል መመራትና እንዲወከልም እንደማይፈቅድ በአጽንኦት እናሳስባለን።

በአካባቢው ምንም ችግር ሳይፈጠር ችግር አለ በማለት በሰላም የምርጫው ሂደት ተጠናቆ የማዳመር ስራው ቆሞ ወደ ፌደራል ተጭኖ የተሸጠውን የህዝብ

ድምጽ እንዲመለስ በሰላሙ የሰላም አምባሳደር ሰላም ወዳድ በሆነው ጋሞ ዞን በቁጫ ህዝብ ስም እንጠይቃለን።

የወረዳችን ህዝብ እስካሁንም ያሳየውን ትዕግሥት በማጠናከር የህግ የበላይነትን በማከበር ድምጻችንን በአግባቡ በመጠየቅ የሚመለከተው አካል ይህንን ጉዳይ በማጣራት የሰላም አምባሳደር የሆነውን ጋሞ ደሬ ቁጫ ህዝብ ትክክለኛውን የመረጡትን ተወካይ እንዲያስቀምጡ በትዕግስት እንድንጠባበቅ እናሳስባለን።

ጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ ከመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት

ህዳር 08/03/2014 ዓ:ም